

ይህ ሥዕል እመቤታችን እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ብላ የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት በተቀበለች ጊዜ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ የምትኾን በከዊን የምትለይ ባሕርይ ያለችው አካለ ቃል ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ሰብአዊ አካልን እንበለ ዘርዕ ነሥቶ ሰው እንደ ኾነ ያሳያል ። ሉቃ ፩፥ ፳፮—፴፰ ።



ዮሐንስ ወንጌሉን ቃል ሥጋ ኾነ እያለ ሲጽፍ ያሳያል ዮሐ ፩ ፲፬ ።



ይህ ሥዕል ፀጎል ተጥሎ በሬሬርቅ ተጠቅሎ አህያና በሬ ትንፋሻቸውን እያሖሖቁት የእናቱን ጡት ሽቶ ሲያለቅስ ያሳያል ። ሉቃ ምዕ፡ ቍ ፯ ።



ይህ ሥዕል መለኮት በሥጋ እንደ ተጠመቀ አብም ይህ ልጄ ነው ብሎ እንደ መሰከረ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል እንደ ወረደ ያሳያል ማቴ ፫—፲፯ ።

